በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት
ኮሚሽን

THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN INVESTMENT
COMMISSION

ቀን 22 ታህሳስ 2007
DATE

ቁጥር ፈ/ኢ4/16/01
REF.No.

ለኢትዮጵያ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን
<u>አዲስ አበባ</u>

ለትግራይ ብ/ክ መንግሥት ከተማ ልማት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ
<u>መቀሌ</u>
ለአፋር ብ/ክ መንግሥት የንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ ትራንስፖርትና ኢንቨስትመንት ቢሮ
<u>ሰመራ</u>
ለአማራ ብ/ክ መንግሥት ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ቢሮ
<u>ባህር ዳር</u>
ለኦሮሚያ ብ/ክ መንግሥት ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>
ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ክልላዊ መንግሥት ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
<u>ሐዋሳ</u>
ለጋምቤላ ብ/ክ መንግሥት ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
<u>ጋምቤላ</u>
ለሐረሪ ብ/ክ መንግሥት ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት
<u>ሐረር</u>
ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/ መንግሥት ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት
<u>አሶሳ</u>
ለኢትዮጵያ ሶማሌ ብ/ክ መንግስት ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
<u>ጅግጅጋ</u>
ለአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
<u>አዲስ አበባ</u>
ለድሬዳዋ የንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ
<u>ድሬዳዋ</u>

ጉዳዩ፡- <u>በአዲስ መልክ የጸደቀውን ለቱሪስት አገልግሎ ሰጪ ድርጅቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ስለመላክ፣</u>

በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 29 ንዑስ ቁጥር 4 መሠረት የኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ ሊያወጣ እንደሚችል በተደነገገው መሠረት ለቱሪስት አገልግሎ ሰጪ ድርጅቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎችን ለመወሰን አዲስ መመሪያ አውጥቷል፡፡

በዚሁ መሠረት መመሪያውን በዚህ ደብዳቤ ሸኚነት የላክን ሲሆን፣ በመመሪያው መሠረት እንዲፈጸም እናሳስበላን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ፍፁም አረጋ
ዋና ዳይሬክተር

አባሪ፡- 1 ጥራዝ መመሪያ

<u>ግልባጭ፡-</u>
- ለኢንቨስትመንት ቦርድ ጽ/ቤት
- ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
- በኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለም/ዋና ዳይሬክተሮች

<u>አዲስ አበባ</u>

ስልክ 011- 551 00 33
Tel. 011-553 72 86

✉ 2313
Website = www. ethioinvest.org
E-mail address = ethiopian.invest@ethioinvest.org

ፋክስ
Fax: 011-551 43 96

# ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎችን ለመወሰን የወጣ የኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ ቁጥር 5/2007

# ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎችን ለመወሰን የወጣ የኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በአገሪቱ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ ለማስተባበርና ለማስፋፋት አዋጅ ቁጥር 769/2004ን /እንደተሻሻለ/ እና ይህንኑ አዋጅ ለማስፈጸም ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የስራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005ን /እንደተሻሻለ/ ያወጣ በመሆኑ፣

በዚሁ ደንብ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ማለትም የኮከብ ደረጃ ላላቸው ሆቴሎች /የሪሶርት ሆቴልን ጨምሮ/፣ ሞቴሎች፣ ሎጆችና ሬስቶራንቶች የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀድ በመሆኑ፣

እንደ ፕሮጀክቱ ስፋት እየታየ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የካፒታል ዕቃዎችን ዓይነትና ብዛት መወሰን በማስፈለጉ፣

የኢንቨስትመንት ቦርድ በኢንቨስትመንት ዓዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 29 /4/ መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል::

## አንቀጽ 1
## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣ የኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ ቁጥር 5/2007 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## አንቀጽ 2
## ትርጓሜ

1. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ:-
   1.1 "የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት" ማለት ስለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 173/2002 መሠረት ሆቴል፣ሞቴል፣ ሎጅ ወይም ሬስቶራንት ማለት ነው። ሆኖም በዚህ መመሪያ ፔንሲዮን እና ከባለ አንድ ኮከብ ደረጃ በታች ያሉ ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች ወይም ሬስቶራንቶች አይሸፈኑም::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Commission

1.2 "ሆቴል"፣ "ሞቴል"፣ "ሎጅ"፣ "ሬስቶራንት" ስለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 173/2002 መሠረት የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ።

1.3 "ሪሶርት ሆቴል" ማለት ለመዝናናት፣ የዕረፍት ጊዜን ለማሳለፍ ወዘተ... ከከተማ ወጣ ብሎ በቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ወይም በመዝናኛ ስፍራዎች የሚቋቋም ዘመናዊ ሆቴል ነው።

1.4 "ዓዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት ዓዋጅ ቁጥር 769/2004 /እንደተሻሻለ/ ነው።

1.5 "ደንብ" ማለት ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የስራ መስኮች የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 /እንደተሻሻለ/ ነው።

2. በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጎች በኢንቨስትመንት ዓዋጁና ደንቡ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ።

## አንቀጽ 3
## የካፒታል ዕቃዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ የሚፈቅድላቸው የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች

1. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጣ ባለሃብት አዲስ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ለማቋቋም ሲፈልግ ወይም ነባር የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በኢንቨስትመንት አዋጁ ላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ማስፋፋት/ማሻሻል ሲፈልግ ወይም በአዋጁ ላይ ከተጠቀሰው ባነሰ ሁኔታ ኢንቨስትመንቱን ማስፋፋት/ማሻሻል ሲፈልግ በዚህ መመሪያ መሠረት ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉትን የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል።

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ለማቋቋም የፈለገ ባለሃብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥቶ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ በሚያደርግበት ወቅት እና የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣ በኋላ ደግሞ ቢያንስ 200 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ወይም በወቅቱ ምንዛሪ ተመጣጣኝ የኢትዮጵያ ብር ኢንቨስት ካደረገ እና ቢያንስ 50 ቋሚ ሠራተኛ የቀጠረ ከሆነ የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር ሆኖ እስከ 5 /አምስት/ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ለድርጅቱ የሚያስፈልጉትን የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል።

## አንቀጽ 4

## ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሚፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎች

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 3 ለተመለከቱት የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀደው የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የኮከብ ደረጃ ለሰጣቸው ወይም እንደሚሰጣቸው በደብዳቤ ላረጋገጠላቸው ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡፡

### ሠንጠረዥ

### የኮከብ ደረጃ ላላቸው ሆቴሎች /የሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ/ ፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች እና ሬስቶራንቶች

### ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀዱ የካፒታል እቃዎች

| ተ.ቁ | የስራ ክፍል | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| 1. | የእንግዳ መቀበያ እና ማረፊያ ክፍል | ➢ ለእንግዳ ማረፊያ የሚሆኑ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች<br>➢ አንድ ቴሌቪዥንን ከነማስቀመጫው<br>➢ አንድ የገንዘብ ካዝና<br>➢ ለእንግዳ መቀበያ ክፍል ሠራተኞች የሚያገለግሉ የማስተናገጃ ዴስኮች፣ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች እና ቁምሳጥን<br>➢ አንድ የማዞሪያ ስልክ ከተጓዳኝ እቃዎቹ ጋር<br>➢ የስልክ ቀፎዎች<br>➢ የሻንጣ፣ የመጽሔት እና የመጽሐፍ ማስቀመጫ እና መያዣ፣<br>➢ የእንግዳ ዕቃ ማጓጓዣ<br>➢ የክፍል ውስጥ አየር መቆጣጠሪያ፣ ማናፈሻ ማቀዝቀዣና ማሞቂያ መሣሪያ<br>➢ የኤሌክትሮኒክስ የበር መክፈቻ ቁልፍ /ቁልፎች/<br>➢ ምንጣፍ እና መጋረጃዎች ከነአክስሰሪያቸው /በክፍሉ ልክ/<br>➢ አንድ የፎጣ ማሞቂያ እና ማቀዝቀዣ ማሽን<br>➢ አንድ ዊልቼር<br>➢ አንድ ዶላር ቼከር ማሽን<br>➢ አንድ የፓስፖርት ስካነር ማሽን<br>➢ አንድ የብር መቁጠሪያ ማሽን<br>➢ አንድ የዕቃ መደርደሪያ<br>➢ አንድ ትልቅ መብራት /ሻንደሊየር/<br>➢ ለእንግዳ ማረፊያ ክፍል ከ4 ያልበለጡ ኮምፒውተሮችና አንድ ፕሪንተር /ለቢዝነስ ሴንተር አገልግሎት የሚውሉ/ |

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Commission

| | | |
|---|---|---|
| 2. | የመመገቢያ ክፍል | ➢ የመመገቢያ ክፍል ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች<br>➢ የቡና ቤት ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች እና በርጩማዎች<br>➢ አንድ የወይን ጠጅ መያዣ እና ማቀዝቀዣ<br>➢ የምግብ እና የመጠጥ ማስተናገጃ ጠረጴዛ፣<br>➢ በግድግዳ ላይ የሚሠራ የዕቃ ማስቀመጫ እና መደርደሪያ<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ የምግብና መጠጥ ማጓጓዣ ጋሪዎች<br>➢ የልጆች ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች<br>➢ የክፍል ውስጥ አየር መቆጣጠሪያ፣ ማናፈሻ፣ ማቀዝቀዣና ማሞቂያ መሣሪያዎች<br>➢ የመጠጥ አገልግሎት መስጫ መሣሪያ፣<br>➢ የዳቦ መጥበሻ መሣሪያ<br>➢ የቡና እና የሻይ ማፍያ መሣሪያ፣<br>➢ የቡና መፍጫ መሣሪያ፣<br>➢ የምግብ መቀላቀያ፣ የፍራፍሬ መጭመቂያ እና የአልኮል መጠጦች መቀላቀያ መሣሪያዎች<br>➢ የእቃ ማጠቢያ ገንዳ<br>➢ የእጅ ማድረቂያ መሣሪያ<br>➢ የዊስኪ ጠርሙስ ማንጠልጠያዎች<br>➢ የበረዶ ቅንጣቶች መስሪያ እና የበረዶ መፍጫ መሣሪያዎች<br>➢ አንድ የዕቃ ማሳያ ካቢኔት፣<br>➢ አንድ የፈንድሻ ማፍኪያ መሣሪያ<br>➢ ምንጣፍ /ከወለሉ ጋር የሚጣበቅ ብቻ/<br>➢ መጋረጃዎች ከነአክስሰሪያቸው /በክፍሉ ልክ/<br>➢ አንድ የኤሌክትሪክ የቡፌ ዲስፕሌይ<br>➢ አንድ ቴሌቪዥን ከነማስቀመጫው<br>➢ አንድ የኮት መስቀያ<br>➢ አንድ የመጠጥ ጠርሙስ ማንጠልጠያ<br>➢ የመጸዳጃ ቤት መስታውት |

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Commission

| | | |
|---|---|---|
| 3. | የእንግዳ መኝታ እና የመታጠቢያ ክፍል | ➢ አልጋዎችና ፍራሾች<br>➢ ቁምሳጥን እና የአልጋ ጎን ኮሞዲኖዎች<br>➢ የልጆች አልጋዎች እና ፍራሾች<br>➢ ምንጣፍ እና መጋረጃዎች ከነአክሰሰሪያቸው /በመኝታ ክፍል ልክ/<br>➢ የመኝታ ክፍል ዕቃዎች /የመጻፊያ ጠረጴዛ፣ የአልጋ ጎን የቡና እና የስልክ ማስቀመጫ ጠረጴዛዎች፣ ሶፋዎች፣ ወንበሮች፣ በርጩማዎች፣ ቁምሳጥኖች እና ባለመሳቢያ የልብስ ማስቀመጫ ኮሞዲኖዎች/<br>➢ የመዋቢያ ጠረጴዛዎች እና መስታወቶች<br>➢ የስልክ ቀፎዎች /የመታጠቢያ ክፍልን ጨምሮ/<br>➢ የእንግዳ ካዝና፣<br>➢ የክፍል ውስጥ አየር መቆጣጠሪያ፣ ማናፈሻ፣ ማቀዝቀዣ እና ማሞቂያ መሣሪያዎች፣<br>➢ መጥሪያ/ደወል/፣<br>➢ የፎጣ መስቀያ፣<br>➢ የሳሙና መያዣ፣<br>➢ የመፀዳጃ ወረቀት መያዣ፣<br>➢ የእሳት አደጋ ጠቋሚና የውኃ መርጫ መሣሪያዎች<br>➢ ጃኩዚ፣ ቴሌፎን ሻወር ከነሙሉ ዕቃዎች<br>➢ ቴሌቪዥን ከነማስቀመጫው<br>➢ መጥፎ ጠረን የሚያስወጣ ፋን<br>➢ ፍሪጅ<br>➢ የሻንጣ ማስቀመጫ<br>➢ የራስጌ መብራቶች<br>➢ የኤሌክትሮኒክስ የበር መክፈቻ ቁልፍ<br>➢ የበር መመልከቻ ሌንስ<br>➢ የቡና እና የሻይ ማሽን<br>➢ የፀጉር ማድረቂያ ማሽን<br>➢ የሙዚቃ ማጫወቻ ስፒከር ስቴሽን<br>➢ የግድግዳ የማንበቢያ የጎን መብራት<br>➢ አላርም ሬዲዮ ባለሰዓት<br>➢ የኮት መስቀያ<br>➢ መተኮሻ ጠረጴዛ ከነካውያው |

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Commission

| | | |
|---|---|---|
| 4. | **የቤት አያያዝ እና የልብስ ንጽሕና መስጫ ክፍል** | ➢ ከአምስት ያልበለጡ ለቤት አያያዝ የሚያገለግል ጋሪዎች /ለሬስቶራንቶች አልተፈቀደም፣ ለሌሎቹ ተፈቅዷል/<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ የወለል ማፅጃ መሣሪያዎች<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ የምንጣፍ ማፅጃ መሣሪያዎች<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ እርጥብና ደረቅ ወለል ማፅጃ መሣሪያዎች<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ የወለል መወልወያዎች ከመጭመቂያዎቻቸው ጋር<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ በኤሌክትሪክ፣ በእንፋሎት ወይም በጋዝ የሚሠሩ የልብስ ማጠቢያ መሣሪያዎች<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ በኤሌክትሪክ፣ በእንፋሎት ወይም በጋዝ የሚሠሩ የልብስ ማድረቂያና መተኮሻ መሣሪያዎች<br>➢ የልብስ መተኮሻ ካውያ ከጠረጴዛው ጋር<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ የልብስ ውሃ መጭመቂያ መሣሪያዎች<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ የቀላል ጨርቃጨርቆችና ልብስ ማድረቂያ መሣሪያዎች<br>➢ ከአምስት ያልበለጡ የልብስ ስፌት መሣሪያዎችየክፍል ውስጥ አየር ማናፈሻ፣ መቆጣጠሪያ መሣሪያ<br>➢ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ<br>➢ የልብስ መደርደሪያ ቁም ሳጥን<br>➢ የደረቅ እጥበት መሣሪያ<br>➢ የሴራሚክ ማጽጃ መሣሪያ<br>➢ የወለል ማብረቅረቂያ መሣሪያ<br>➢ የላውንደሪ የእንግዳ ልብስ መስያ መሣሪያ |

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Commission

| | | |
|---|---|---|
| 5. | የምግብ ማዘጋጃ እና ማከማቻ ክፍል | ➢ የጋዝ ወይም የኤሌክትሪክ ምድጃዎች<br>➢ በጋዝ ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል ግሎ ለምግብ ማብሰያነት የሚያገለግል የብረት ግሪል<br>➢ የተለያዩ ክፍሎች ያሉት የማብሰያ መሣሪያ<br>➢ የዳቦ መጥበሻ መሣሪያ<br>➢ የውሃ ማሞቂያ<br>➢ በዝግታ ማብሰያ መሣሪያ<br>➢ የመቁያ መሣሪያ<br>➢ የስጋ መፍጫ እና የሥጋና አጥንት መቁረጫ መሣሪያ<br>➢ የምግብ ቅርፅ መስጫ መሣሪያ<br>➢ የዳቦ መጋገሪያ መሣሪያና ትሪዎች<br>➢ የምግብ ማዘጋጃ ጠረጴዛ<br>➢ የኬክ መስሪያ መሣሪያ<br>➢ የአይስክሬም መስሪያ መሳሪያ<br>➢ የምግብ መቀላቀያ/መደባለቂያ መሣሪያ<br>➢ የማእድ ቤት ሚዛን<br>➢ የኑድል / የቀጭን ፓስታ ወይም የላዛኛ ወይም የሪቪዮሊ/ ማዘጋጃ መሣሪያ<br>➢ መደበኛ እና/ወይም ግዙፍ ማቀዝቀዣ<br>➢ የዕቃ /የሳህን፣ የብርጭቆ እና/ወይም የስኒ/ ማጠቢያ መሣሪያ<br>➢ የእቃ ማጠቢያ ገንዳ/ሲንክ ከተጓዳኝ እቃዎች ጋር<br>➢ ማቀዝቀኝያ ቤት፣<br>➢ የእቃ ማስቀመጫ መደርደሪያዎች<br>➢ የሳህን ማሞቂያ መሣሪያ፣<br>➢ የምግብ ማዘጋጃ ገበታ፣<br>➢ የክፍል ውስጥ አየር መቆጣጠሪያ፣ ማናፈሻ፣ ማቀዝቀዣና ማሞቂያ መሣሪያዎች<br>➢ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ<br>➢ የጭስ ማውጫ መሣሪያ (Hood)<br>➢ የዳቦ ማኩፈሻ፣ ማቡኪያና መዳመጫ መሣሪያ<br>➢ የእንቁላል መቀላቀያ መሣሪያ<br>➢ የምግብ እና የፍራፍሬ መፍጫ መሣሪያ<br>➢ የድንች መጥበሻ መሣሪያ<br>➢ የፒዛ መጋገሪያ መሣሪያ<br>➢ የዶሮ መጥበሻ መሣሪያ<br>➢ የምግብ ማሞቂያ መሣሪያ<br>➢ የሾርባ ማሞቂያ መሣሪያ |

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Investment Commission

| | | |
|---|---|---|
| 6 | የግብዣ እና የመሰብሰቢያ አዳራሽ | ➢ የስብሰባ ወንበሮችና ጠጴዛዎች<br>➢ መነጋገሪያ መሳሪያዎች<br>➢ አዶቪዥዋል መሳሪያዎች<br>➢ የድምጽ ኢቫኩየሽን ሲስተም<br>➢ የትርጉም ማስተላለፊያ መሳሪያዎች<br>➢ የክፍል ውስጥ አየር መቆጣጠሪያ፣ ማናፈሻ ማቀዝቀዣና ማሞቂያ መሣሪያዎች<br>➢ አዳራሹ ውስጥ በቋሚነት የሚተከል ፕሮጀክተር<br>➢ አንድ ቴሌቪዥን ከነማስቀመጫው<br>➢ ምንጣፍ እና መጋረጃዎች /በአዳራሹ ልክ/ |
| 7 | የፊዚዮ-ቴራፒ፣ የስፖርትና የመዝናኛ አገልግሎት መስጫ ክፍል | ➢ በቤት ውስጥ ለሚደረጉ ስፖርታዊ ልምምዶች የሚያስፈልጉ የጅምናዚየም መሣሪያዎች<br>➢ የስቲም ባዝ አገልግሎት መስጫ መሣሪያ<br>➢ የሳውና እና/ወይም የጃኩዚ አገልግሎት መስጫ መሣሪያ<br>➢ አንድ ቴሌቪዥን ከነማስቀመጫው |
| 8 | የመዋኛ ስፍራ | ➢ የውሃ መምጠጫ መሣሪያ፣<br>➢ በመዋኛ ስፍራ ለማረፊያ የሚያገለግሉ ወንበሮች/መንጋለያዎች፣<br>➢ የመዋኛ ውሃ ማጥሪያ መሣሪያ<br>➢ የእንግዳ ዕቃ ማስቀመጫ ሎከር<br>➢ የቁም ሻወሮች |

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን * The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Commission *

| | | |
|---|---|---|
| 9 | የውበት መጠበቂያ ክፍል አገልግሎት | ➢ የማሳጅ አልጋዎች<br>➢ የፎጣ ማሞቂያ ማሽን<br>➢ የክፍል ማሞቂያና ማቀዝቀዣ መሣሪያ<br>➢ የስቲም ባዝ፣ የሳውና እና/ወይም የጃኩዚ አገልግሎት መስጫ<br>➢ የእንግዳ መቀበያ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች<br>➢ የእንግዳ ልብስ ማስቀመጫ ሎከር |
| 10 | ተዛማጅ አገልግሎቶች | ➢ ጀነሬተር<br>➢ የውሃ ፓምፕ<br>➢ ለባዮ ጋዝ ማብላያ ግንባታ የሚውሉ የካፒታል ዕቃዎች<br>➢ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች<br>➢ የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያ መሣሪያዎች /የእሳት አላርም/<br>➢ የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና ዕርዳታ መስጫ መሣሪያዎች<br>➢ በማዕከላዊ ቦታ የሚቀመጡ የደህንነት መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች እና/ወይም ካሜራዎች ከተጓዳኝ እቃዎች<br>➢ የሰውና የሻንጣ መፈተሻ መሣሪያዎች<br>➢ በእጅ የሚያዙ የሰው መፈተሻዎች<br>➢ የህንጻ እና የንብረት ማኔጅመንት ሲስተም ከነአክሰሰሪው<br>➢ የመኪና መፈተሻ መስታወት<br>➢ የሠራተኛ የጣት አሻራ መቆጣጠሪያ መሣሪያ<br>➢ የበር ካርድ ሪደር |

## አንቀጽ 5

## ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው የሚገቡ ዕቃዎች ብዛት አወሳሰን

1. ከላይ በሠንጠረዡ የተገለጹት በጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻው የሚፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎች መጠን/ብዛት የሚወሰነው፡-

   1.1. የመኝታና መታጠቢያ ክፍል ቁሳቁሶችና ዕቃዎች በየክፍሎቹ ኘላንና ብዛት መሠረት ነው፡፡

   1.2. ከመኝታና መታጠቢያ ክፍል ውጭ ላሉት ቁጥራቸው በየዕቃዎቹ ትይዩ ላልተጠቀሱ ሌሎች ቁሳቁሶች በማስተናገድ አቅማቸው /ለምሳሌ ለስብሰባ አዳራሽ የሚያስፈልጉ ወንበሮች በአዳራሹ ዲዛይን በሚይዘው ተሳታፊ ብዛት፣ ወዘተ/ መሠረት ይሆናል፡፡

2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ከተመለከቱት የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መካከል በአንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት የካፒታል እቃዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት ባለሀብቱ፡-

   2.1. መሬት ስለማግኘቱ /ሕንፃ ተከራይቶ ወይም ገንብቶ ከሆነ 80 ከመቶ ግንባታው መጠናቀቁን/ ሕጋዊ ማስረጃ፣

   2.2. ኘሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት፣ መሠረተ-ልማት፣ መጋዘን፣ መንገድ እና የመሳሰሉት ስራዎች እየተከናወኑ ስለመሆናቸው ከፌዴራል ወይም ከክልል የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት የተሰጠውን ማስረጃ፣

   2.3. ለኘሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል እቃዎች ከውጭ አገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (AirWay Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Truck Way Bill ) እና የግዥ ደረሰኝ ( Commercial Invoice) ወይም የካፒታል እቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግዥ ደረሰኝ ከአስፈላጊ ማስረጃዎች ጋር፣

   2.4. የካፒታል እቃው በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሠነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ ባለሀብቱ በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ ( Bank Statement)

   2.5. የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ/ኘሮጀክቱ በደንብ ቁጥር 173/2002 በተደነገገው መሠረት የሚጠበቅበትን የባለኮከብ ደረጃ መስፈርት ስለማሟላቱ/እንደሚያሟላ የሚገልጽ ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የተጻፈ የድጋፍ ደብዳቤ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Commission

## አንቀጽ 6
## የማስፋፊያ/የማሻሻያ ኢንቨስትመንቶች

በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 3 ከተዘረዘሩት የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መካከል በአንዱ ወይም ከአንዱ በላይ የተሠማራ እና በኢንቨስትመንት ዓዋጁ መሠረት ነባር ድርጅቱን ያስፋፋ/ያሻሻለ ባለሀብት የማስፋፊያ/የማሻሻያ ፕሮጀክቱ እንደ አዲስ ፕሮጀክት ተቆጥሮ አግባብነት ያላቸውን በሠንጠረዡ የተመለከቱትን የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

## አንቀጽ 7
## መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቦርዱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ 8
## ተፈጻሚነት ስለሌለው መመሪያ

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 9
## መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመስከረም 01 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Investment Commission

--------------------
መኮንን ማንያዘዋል
የኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢ